


በፕሬዘደንት ቶማስ ኤስ ሞንሰን

# የእግርህን መንገድ አቅና

***ወደ ኢየሱስ እንደ ምሳሌአችን ስንመለከት እና የእርሱን እርምጃዎች ስንከተል፣ ወደ ሰማይ አባታችን ለዘለአለም ከእርሱ ጋር አብሮ ለመኖር በደህንነት ለመመለስ እንችላለን።***

ውድ ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ በዚህ ጠዋት በእናንተ ፊት ስቆም ትህትና ይሰማኛል። ከእናንተ ጋር ይህን መልእክት ስካፈል፣ የእናንተ እምነት እና ጸሎት ከእኔ ጋር እንዲሆን እጠይቃለው።

ሁላችንም የመንፈስ አለምን ትተን በአብዛኛው አስቸጋሪ በሆነ ሟችነት ተብሎ ወደሚጠራው ደረጃ ስንገባ አስደናቂና አስፈላጊ የህይወትን ጉዞ ጀምረናል። በምድር የምንገኝባቸው ዋና ምክንያቶችም የስጋና የአጥንት ሰውነትን ለማግኘት፣ ከሰማይ ወላጆች በመለየት ብቻ የሚገኘውን አጋጣሚዎች ለማግኘት፣ እና ትእዛዛትን እንደምንጠብቅ ለማወቅ ናቸው። በመፅሐፈ አብርሐም ምዕራፍ 3 እንደምናነበው፣ "እናም ጌታ አምላክ የሚያዛቸውን ማናቸውንም ነገሮች ሁሉ እንደሚያደርጉ ለማየት፣ በዚህ እንፈትናቸዋለን።"[1]

ወደ ምድር ስንመጣ፣ ከእግዚአብሔር ታላቅ ስጦታዎችን ይዘን መጣን–ይህም ነጻ ምርጫ ነው። በብዙ ሺህ መንገዶች ለራሳችን ለመምረጥ እድለኞች ነን። እዚህ ከአስቸጋሪው የልምድ የተግባር አለቃ  እንማራለን። በመልካም እና ክፉ መካከል ልዩነትን እናውቃለን። በጣፋጭ እና በመራራው መካከልም ልዩነትን እናገኛለን። ውሳኔ እጣ ፈንታን እንደሚወስንም እንማራለን።

እርሱ ለእኛ ያለመውን፣ እና እኛ በጣም የምንፈልገውን፣ ዘለአለማዊነትን ለማግኘት እንድንችል ወደ እርሱ ለመመለስ ሀይለኛ የሆነ ፍላጎት እያለን አባታችንን ትተን እንደሄድን እርግጠኛ ነኝ። ወደ ሰማይ አባታችን የሚመልሰውን መንገድ ለማግኘት እና ለመከተል ሀላፊነት ቢኖርብንም፣ ያለመመሪያ እና አቅጣጫ አልላከንም። ይልቁንም፣ የሚያስፈልገንን መሳሪያዎች ሰጥቶናል፣ እናም እስከመጨረሻ ለመፅናት እና የዘለአለም ህይወት ለማግኘት የእርሱን እርዳታ ስንፈልግ እና በሙሉ ኃይላችን ስንጥር እርሱም ይረዳናል።

እንዲመራ ለመርዳት በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ የእግዚአብሔር እና የልጁ ቃላት አሉን። የእግዚአብሔር ነቢያት ምክሮች እና ትምህርቶች አሉን። ከሁሉም በላይ፣ የምንከተለው ፍጹም የሆነ ምሳሌ፣ —ማለትም የጌታችን እና  የአዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ —ተሰጥቶናል፣ እናም ያን ምሳሌ እንድንከተል መመሪያ ተሰጥቶናል። አዳኙ እራሱ "ኑ ተከተሉኝ" ብሏል።[2] "ስሰራ ያያችሁትን እንዲሁ ስሩት።"[3] ይህን ጥያቄንም አቅርቧል፣ "እናንተ ምን ዐይነት ሰዎች ትሆኑ ዘንድ ይገባችኋል?" ከዚያም እንዲህ መለሰ"እውነት እላችኋለሁ እንደ እኔ ሁኑ።"[4] "መንገዱን አመላከተ እናም በመንገዱንም መራ።"[5]

ወደ ኢየሱስ እንደ ምሳሌአችን ስንመለከት እና የእርሱን እርምጃዎች ስንከተል፣ ወደ ሰማይ አባታችን ለዘለአለም ከእርሱ ጋር አብሮ ለመኖር በደህንነት ለመመለስ እንችላለን። ነቢዩ ኔፊ እንዲህ አለ፣ "የህያው እግዚአብሔርን ልጅ ምሳሌንበመከተል ሰው እስከመጨረሻው የማይፀና ከሆነ፣ መዳን እንደማይችል በዚህ አውቃለሁ።"[6]

አንድ ሴት፣ ቅዱስ ምድርን ስለጎበኘች በት አጋጣሚዋን በምትናገርበት ጊዜ ሁሉ፣ እንዲህ ትል ነበር፣ "ኢየሱስ በተራመደበት ተራመድኩኝ!።"

ኢየሱስ በኖረበት እና በአስተማረበት አካባቢዎች ነበረች። ምናልባትም እርሱ ቆሞበት በነበረው አለት ላይ ቆማ ወይም የተመለከተውን ተራራዎች ተመልክታ ይሆናል። ያም አጋጣሚ በብቻው ለእርሷ በጣም አስደሳች ይሆናሉ፤ ነገር ግን በአካል እርሱ *በተራመደበት መራመድ* እርሱ *እንደተራመደው ከመራመድ* ያነሰ ጥቅም ያለው ነው። እርሱ ያደረገውን ማድረግ እና ምሳሌውን መከተል በስጋ ህይወቱ እርሱ የተጓዛቸውን መንገዶች ከመከተል በላይ በጣም አስፈላጊ ናቸው።

ኢየሱስ ለአንድ ሀብታም ሰው "ና ተከተለኝ"[7] የሚለውን ግብዣ ሲሰጠው፣ ሀብታሙ ሰው በኮረብታው እና በሸለቆው ወደላይ እና ወደታች ሲሄድ ከኋላው እንዲከተለው ፈልጎ አልነበረም።

ኢየሱስ በተራመደበት ለመራመድ በገሊላዳር ወይም  በይሁዳ ኮረብታዎች ላይ መጓዝ የለብንም። የእርሱ ቃሎች በጆሯችን ውስጥ እየደወሉ፣ መንፈሱ ልባችንን እየሞላው፣ እና ትምህርቶቹ ህይወታችንን እየመሩት፣ በሟችነት ህይወት ውስጥ ስንጓዝ እርሱን ለመከተል ስንመርጥ፣ እርሱ በተጓዘበት መንገድ ለመጓዝ እንችላለን። ምሳሌው መንገዱን ያበራል። እንዲህም ብሏል፣ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ።"[8]

ኢየሱስ የተጓዘውን መንገድ ስንፈትሽ፣ በዚህ ህይወት ውስጥየሚያጋጥመን አይነት ብዙ ተመሳሳይ ፈተናዎችን እንደወሰደ እንመለከታለን።

ለምሳሌ፣ ኢየሱስ የሚያስከፋ መንገድን ተጉዟል። ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጡ መንገዶችን ቢጓዝባቸውም፣ ለህዝብ የሚሰብክበትን በሚፈጽምበት ጊዜ ስለኢየሩሳሌም ያለቀሰበት ከሁሉም በላይ ልብን የሚነካ ነበር። የእስራኤል ልጆች ደህንነት የሚሰጠውን የክንፉን ጥበቃ አንቀበልም ብለው ነበር። በቅርብ በጥፋት የሚተወውን ከተማ እየተመለከተ ሳለ፣ ጥልቅ በሆነ የሀዘን ስሜት ተሸንፎ ነበር። በስቃይም

እንዲህ አለቀሰ፣ “ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፥ እናንተም አልወደዳችሁም።”[9]

የፈተናን መንገድ ኢየሱስም ተጉዟል። ክፉው ሉሲፈር ታላቅ ጥንካሬውን፣ የሚያጓጓውን ውሸቶቹን ሰብስቦ፣ ለ40 ቀን እና 40 ምሽት የጾመውን ፈተነው። ኢየሱስ አልወደቀም፣ ይልቁንም እያንዳንዱን ፈተና ተቋቋመ። የመጨረሻው ቃላትም፣ “ሂድ፥ አንተ ሰይጣን” ነበር።[10]

ኢየሱስ የህመም መንገድን ተጉዟል። በገትሰመኔ “ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ” በሆነበት ጊዜ ስለነበረው ነገር አስቡበት።[11] እናም በመስቀል ላይ የተሰቃየበትን ማንም አይረሳም፡ ፡

እያንዳንዳችን ምናልባት ባመለጠን እድል፣ በአግባቡ ባልተጠቀምነው ኃይል፣ በምናፈቅረው ሰው ምርጫ፣ ወይም እራሳችን በምናደርጋቸው ምርጫ ምክንያት የተስፋ መቁረጥ መንገድን እንጓዛለን። የፈተና መንገድም የእያንዳንዳችን መንገድ ይሆናል። በትምህርት እና ቃል ኪዳን ክፍል 29 ውስጥ እንደምናነበው፥ “እናም ሰይጣን የሰዎችን ልጆች ይፈትን ዘንድ ግድ ነው፣ ይህ ካልሆነ በራሳቸው መምረጥ አይችሉምና።”[12]

የህመም መንገድንም እንደዚሁ እንጓዛለን። እኛ እንደ አገልጋዮች፣ ከታላቅ ህመም እና ስቃይ በኋላ የስጋ ህይወትን ትቶ ከሄደው መምህር በላይ ለመጠበቅ አንችልም።

በመንገዳችን መራራ ሀዝን ብናገኝም፣ ታላቅ ደስታንም ለማግኘት እንችላለን።

እኛም ከኢየሱስ ጋር የታዛዥነትን መንገድ ለመጓዝ እንችላለን። ሁልጊዜም ቀላል አይደለም፣ ነገር ግን መፈክራችን በሳሙኤል እንደ ውርስ የተሰጠን ይሁን፥ “እነሆ፥ መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብከማቅረብ ይበልጣል።”[13] ታዛዥ ያለመሆን የመጨረሻ ውጤት ባርነትና ሞት ነው፣ ግን የታዛዥነት ሽልማት ነጻነትና የዘለአለም ህይወት ነው።

እኛ እንደ ኢየሱስ የአገልግሎት መንገድን መጓዝ እንችላለን። በሰዎች መካከል ሲያገለግል የነበረው የኢየሱስ ህይወት በሀይል እንደሚያበራ ብርሀን አይነት ነው። በአካለ ስንኩል እጅና እግሮች ላይ ጥንካሬ፣ በአይነ ስውር ላይ ማየት፣ በደንቆሮም መስማትን አመጣ።

ኢየሱስ የጸሎት መንገድን ተጉዟል። እንደ ጌታ ጸሎት የምናውቀውን ውብ ጸሎት በመስጠት እንዴት መፀለይ እንደምንችል አስተማረን። በገትሰመኔ የነበረውን ጸሎትስ ማን ይረሳል፥ “የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ”?[14]

በጌታ የተሰጡን ሌሎች መመሪያዎች በጣቶቻችን ጫፍ ላይ፣ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ይገኛሉ። በተራራ ላይ ባስተማራቸው፣ ሩህሩህ፣ ትሁት፣ ጻድቅ፣ በልብ ንጹህ፣ ሰላም ፈጣሪዎች እንድንሆን ነገረን። ቢሳለቁብን እና ቢያሳድዱንም፣ ለሀይማኖታችን በጀግንነት እንድንቆም መመሪያ ሰጥቶናል። ሌሎች እንዲመለከቱ እና የሰማይ አባታችንን ለማሞገስ ፍላጎት እንዲኖራቸው ብርሀናችንን እንድናደምቅ ጠይቆናል። በሀሳባችንና በስራችን ምግባረ መልካም እንድንሆን አስተምሮናል። ከሁሉም በላይ አስፈላጊ የሚሆነውንም ከምድር በላይ በሰማይ ሀብታችንን እንድናከማች ነግሮናል።[15]

ምሳሌዎቹ በሀይል እና በስልጣን ያስተምራሉ። በመልካሙ ሰማሪያ ታሪክም ጎረቤቶቻችንን እንድንወድ እና እንድናገለግል አስተምሮናል።[16] በመክሊት ምሳሌውም እራሳችንን እንድናሻሽል እና ፍጹም ለመሆን እንድንጥር አስተምሮናል።[17] በጠፋው በግ ምሳሌም ከመንገዱ የወጡትን እና መንገዳቸው የጠፋባቸውን እንድናድን መመሪያ ሰጥቶናል።[18]

ቃላቱን በመማር፣ ያስተማራቸውን በመከተል፣ እና በተጓዘበት በመራመድ ክርስቶስን የህይወታችን መሀከል ለማድረግ ስንጥር፣ ለማግኘት የሞተበትን የዘለአለም ህይወት ከእኛ ጋር ለመካፈል ቃል ገብቷል። የእርሱን መርህ ከመቀበል እና የእርሱ ደቀመዛሙርት ከመሆንና በህይወታችን ሙሉ ስራውን ከማከናወን በላይ የሆነ ምንም ከፍተኛ ነገር የለም። ምንም ነገር፣ ምንም የምናደርጋቸው ምርጫዎች እርሱ ሊያደርገን ከሚችለው በላይ ሊያደርጉን አይችሉም።

የአዳኝን ምሳሌ ለመከተል እና በመንገዱ ለመራመድ በእውነት ስለሞከሩት ሳስብ፣ የጉስታፍና ማርጋሬት ዋከር— ስም በአዕምሮዬ ይመጣል–እነርሱም ከማውቃቸው በላይ እንደ ክርስቶስ አይነት የሆኑ ሰዎች ናቸው። የጀርመን አገር ሰዎች ሆነው ወደ ካናዳ የተሰደዱ ነበሩ፣ እናም እንደ ሚስዮን ፕሬዘደንት ሳገለግል ነበር የተገናኘኋቸው። ወንድም ዋከር መኖሪያውን የሚያገኘው ጸጉር በመቁረጥ ነበር። ብዙ ገንዘብ ባይኖራቸውም፣ ያላቸውን ሁሉ ያካፈሉ ነበር። በልጆች አልተባረኩም ነበር፣ ነገር ግን በቤታቸው የገቡትን ሁሉ ይንከባከቡ ነበር። የተማሩና የሰለጠኑ ወንዶች እና ሴቶች እነዚህን ትሁት፣ ያልተማሩ የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ይፈልጉ እና በእነርሱ ፊት አንድ ሰዓት ማሳለፍ ከቻሉ ራሳቸውን እንደ እድለኛ ይመለከቱ ነበር።

አመለካከታቸው ልዩ አልነበረም፣ እንግሊዝኛቸው ፍጹም ያልሆነና ለመረዳት የሚያስቸግር፣ ቤታቸው መጠነኛ ነበር። መኪና ወይም ቴሌቪዥን አልነበራቸውም፣ አለም ትኩረት የሚሰጣቸውን ማንኛቸውን ነገሮችን አላደረጉም። ነገር ግን ታማኞች በዚያ የሚገኘውን መንፈስ ለመካፈል ወደ እነርሱ ይመጡ ነበር። ቤታቸው በምድር እንደ ሰማይ ነበር፣ እናም መንፈሳቸው ንጹህ ሰላም እና መልካምነት ያንጸባርቅ ነበር።

የአዳኝን መንገድ ስንራመድ እና የእርሱን ፍጹም ምሳሌ ስንከተል እኛም ያን መንፈስ ሊኖረን እና ይህን ከአለም ጋር ለመካፈል እንችላለን።

በምሳሌ ውስጥ ይህን ምክር እናነባለን፣ “የእግርህን መንገድ አቅና።”[19] ይህን ስናደርግ፣ ኢየሱስ የተጓዘበትን ለመጓዝ እምነት፣ እንዲሁም ፍላጎት ይኖረናል። የሰማይ አባታችን እንድንከተለው በሚፈልገው መንገድ ላይ እንዳለን ምንም ጥርጣሬ አይኖረንም። አዳኝ ለምናደርጋቸው ነገሮች በሙሉ መመሪያ የሚሆን ምሳሌ ይሰጣል፣ እናም ቃላቱ ሊወድቁ የማይችሉ መመሪያዎች ይሰጣሉ። መንገዱ በደህንነት ወደ ቤት ይወስደናል። ይህም በረከታችን እንዲሆን የምጸልየው፣ በማፈቅረው፣ በማገለግለው፣ እናም ስለእርሱ በምመሰክረው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።


ማስታወሻዎች
1. Abraham 3፥25
2. ሉቃስ 18፥22
3. 3 ኔፊ 27፥21።
4. 3 ኔፊ 27፥27።
5. ኢላይዛ አር. ስኖው, “How Great the Wisdom and the Love,” *መዝሙሮች*, ቁጥር. 195
6. 2 ኔፊ 31፥16
7. ሉቃስ 18፥22
8. ዮሀንስ 14፥6
9. ሉቃስ 13፥34
10. ማቴዎስ 4፥10
11. ሉቃስ 22፥44
12. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 29፥39
13. 1 ሳሙኤል 15፥22
14. ሉቃስ 22፥42
15. ማቴዎስ 5፣ 6 ተመልከቱ
16. ሉቃስ 10፥30–37ተመልከቱ
17. ማቴዎስ 25፥14–30ተመልከቱ
18. ሉቃስ 15፥4–7 ተመልከቱ
19. ምሳሌ 4፥26

# የጊዜአችን ትምህርቶች

ከጥቅምት 2014 (እ.አ.አ) እስከ ሚያዝያ 2014 (እ.አ.አ)፣ በአራተኛው እሁድ የመልከፀዴቅ ክህነትና የሴቶች መረዳጃ ማህበር ትምህርቶች ከጥቅምት 2014 (እ.አ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ ከተሰጠው አንድ ወይም ብዙ ንግግሮች ውስጥ መዘጋጀት አለባቸው በሚያዝያ 2015 (እ.አ.አ) ንግግሮች ከጥቅምት 2014 (እ.አ.አ) ወይም ከሚያዝያ 2015 (እ.አ.አ) አጠቃላይ ጉባኤ ይመረጣሉ። የካስማና የአውራጃ ፕሬዘደንቶች በአካባቢያቸው ውስጥ የትኞቹን ንግ ግሮች መጠቀም እንዳለባቸው መምረጥ አለባቸው። ወይም ይህን ሀላፊነት ለኤጲስ ቆጶሶችና ለቅርንጫፍ ፕሬዝደንቶች ማስተላለፍ ይችሉ ይሆናል።

እነዚህ ንግግሮች (በብዙ ቋንቋዎች) በ conference.lds.org ውስጥ ይገኛሉ።

© 2014 በ Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ)
*First Presidency Message, November 2014.* Amharic. 10871 506 ትርጉም



**በፕሬዘደንት ዲየትር ኤፍ ኡክዶርፍ**
*የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ*

# የብርሀን እና እውነት ምስክርነቶችን መቀበል

***ስለብርሀን እና እውነት ያላችሁ የግል ምስክር እናንተን ብቻ ሳይሆን ትውልዳችሁንም በስጋዊ ህይወት ይባርካል፣ ነገር ግን ይህም በዘለአለም ሁሉ አብሯችሁ ይገኛል።***

እንደ አውሮፕላን አብራሪ፣ በጭለማ ክፍለ አህጉሮችን እና ባህሮችን በመሻገር ለብዙ ሰአት በአውሮፕላን እበር ነበር። በአውሮፕላኑ መስኮት የምሽቱን ሰማይ ፣ በተለይም ከዋክብቶችን ስመለከት፣ አብዛኛውን ጊዜ ቅዱሳት መጻህፍቶች "ለመቆጠር የማይቻሉ አለማት" ብለው ስለሚገልጿቸው ስለእግዚአብሔር ፍጥረትታላቅነት እና ጥልቅነት እገረማለሁ።[1]

ከአንድ መቶ አመት በታች በሆኑ ጊዜዎች ከዋክብቶችን የሚያጠኑ ሰዎች በሁለንተና ውስጥ የሚገኙት በሰማይ የምንመለከታቸው ከዋክብቶች ብቻ ናቸው ብለው ያምኑ ነበር።[2] ከምንመለከታቸው ከዋክብቶች ባሻገር ያሉት ነገሮች ታላቅ ምንምነት፣ መጨረሻ የሌለው ባዶ፣ የሚበርድ፣ እና የከዋክብቶች ባዶ፣ ብርሀን፣ እና ህይወት የሌላቸው ናቸው ብለው ያስቡ ነበር።

አጉልቶ የሚያሳዩ መነጽሮች፣ እንዲሁም ወደ ሰማይ በሮኬት የሚላኩት ቴሌስኮፖች—የበለጠ የተወሳሰቡ ሆኑ— ከዋክብትን የሚያጠኑት የሚያስደንቅ፣ ለመረዳት የማይቻል እውነትን ማግኘት ጀመሩ፥በስነ-ፍጥረት ውስጥ ስላሉት በሙሉ ማንም ሰው ከዚህ በፊት ካመኑበት በላይ በአዕምሮ ለመታሰብ ከሚቻልበት በላይ ትልቅ እንደሆነ፣ እናም ሰማይ መቆጠር በማይቻሉ፣ ከእኛ በጣም በራቁ፣ እናም ብዙ መቶ ሚልዮን የሆኑ ከዋክብቶች የሚገኙበት እንደሆነ አወቁ።[3]

በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ በስነ-ፍጥረት ውስጥ ስላሉት በሙሉ ያለን እውቀት ለዘለአለም ተቀየረ።

ዛሬ እነዚህን በርቀት ያሉትን ከዋክብቶች ለማየት እንችላለን።[4]

በዚያም እንዳሉ እናውቃለን።

በዚያም ለረጅም ጊዜ ነበሩ።

ሰው የሰማይን ብርሀኖች ለመሰብሰብ እና እነዚህን ከዋክብቶች እንዲታዩ ለማድረግ ሀይለኛ መሳሪያዎች ከመኖሩ በፊት ፣ እነዚህ ነገሮች ይቻላሉ ብለን አናምንም ነበር።

የሁለንተና ታላቅነት በድንገት አልተለወጠም፣ ነገር ግን ይህን እውነት የማየትና የመረዳት ችሎታችን በጣም ተቀየረ። ከዚያ ታላቅ ብርሀን ጋር፣ ሰው ከዚህ በፊት በአዕምሮአችን ተመልክተናቸው ከማናውቃቸው አስገራሚ ሰፊ እይታ ጋር ተዋወቀ።

## ለማየት የማንችለውን ማመን ከባድ ነው

በጊዜ ወደኋላ በመሄድ ከአንድ ሺህ ወይም ከአንድ መቶ አመት በፊት ይኖር ከነበረ ሰው ጋር ለመነጋገር እንደምትችሉ አስቡ። እኔ እና እናንተ በአሁን ጊዜ የሚገኙትን ችላ የምንላቸውን አንዳንድ ቴክኖሎጂዎች ለእነርሱ ለመግለጽ ስንሞክር አስቡ። ለምሳሌ፣ እነዚህ ሰዎች ስለ ትልቅ አውሮፕላኖች፣ ስለማይክሮዌቭ፣ ብዙ ነገሮችን ለማከማቸት ስለሚችል በእጅ ስለሚያዙ መሳሪያዎች፣ እና ስለልጅ ልጆቻችን በአለም ከሚገኙ ብዙ ሚልዮኖች ጋር ለመካፈል ስለምንችላቸው ስለቭድዮ ታሪኮች ብንነግራቸው እነዚህ ሰዎች ስለእኛ ምን ያስቡ ነበር።

አንዳንዶች ያምኑን ይሆናል። አንዳንዶች ይሳለቁብን፣ ይቃወሙን፣ ወይም ምናልባት እኛን ዝም ለማድረግ ወይም እኛን ለመጉዳት ይፈልጉም ይሆናል። አንዳንዶች እኛ የተሳሳተ አመለካከት እንዳለን፣ ሞኞች፣ ወይም እንዲሁም አደገኛ እንደሆንን ለማሳየት የሚያውቁትን ሎጂክ፣ ምክንያት እና እውነት ለመጠቀም ይሞክራሉ። ሌሎችን ለማሳሳት በመሞከራችን ሊያወግዙን ይችሉ ይሆናል።

ነገር ግን በእርግጥ፣ እነዚህ ሰዎች በሙሉ ይሳሳታሉ። መልካም እና ቅን አስተሳሰብ ያላቸውም ሊሆኑ ይችላሉ። በአስተያየታቸው ትክክል እንደሆኑም ይሰማቸው ይሆናል። ነገር ግን በግልጽ ለማየት በምንም አይችሉም ምክንያቱም ፍጹም የሆነ የእውነት ብርሀንን ገና አልተቀበሉምና።

## የብርሀን ቃል ኪዳን

ስህተተኛ ስንሆንም ትክክለኛ ነን ብሎ ማሰብ የሰው ጸባይ የሆነ ይመስላል። እናም ጉዳዩ ይሄ ከሆነ፣ ለማንኛችንም ምን አይነት ተስፋ አለ። እኛ በራሳችን አስተያየት ከገጠምናቸው በደንብ ባልተሰሩ መሰረቶች ላይ ሆነን፣ በማይስማሙ መረጃዎች ያለመመሪያ እንወዛወዛለን?

እውነትን ለማግኘት ይቻላልን?

የመልእክቴ አላማ እግዚአብሔር ራሱ—ሁሉን እውነት የሚያውቀው የሰራዊት ጌታ—ለልጆቹ እውነትን ለራሳቸው ማወቅ እንደሚችሉ ቃል ኪዳን እንደገባላቸው አስደሳች መልእክት ለማወጅ ነው።

የዚህን ቃል ኪዳን ታላቅ ነት እባካችሁ አስቡ።

ዘለአለማዊው እና ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር፣ የዚህ ታላቅበስነ-ፍጥረት ውስጥ ያሉት በሙሉ ፈጣሪ፣ ወደ እርሱ በቅንልብ እና በእውን ሀሳብ ከሚቀርቡት ጋር ይነጋገራል።

በህልሞች፣ በራዕዮች፣ በሀሳቦች፣ እና በስሜት ይናገራል።

ለመሳሳት በማይቻል እና ከሰው አጋጣሚ በላይ በሆነ መንገድም ይናገራል። መለኮታዊ መመሪያ እና ለግል ህይወታቸው መልሶች ይሰጣል።

በእርግጥም፣ እነዚህ ነገሮች የሚሆኑ አይደ ሉም፣ እግዚአብሔር ካለ የአንድ ሰውን ጸሎት ከመስማት እና ከመመለስ በላይ የሚሻል ነገር ያደርጋል ብለው የሚሳለቁም አሉ።

ነገር ግን ይህን እነግራችኋለሁ፥ እግዚአብ ሐኢር ስለእናንተ ያስባል። ያዳምጣል፣ እናም የግል ጥያቄአችሁን ይመልሳል። ለጸሎታችሁ መልሱ በራሱ መንገድና በራሱ ሰዓት ይመ ጣል፣ እናም ስለዚህ ፣ ድምጹን ለማዳመጥ መማር አለባችሁ። እግዚአብሔር ወደ እርሱ መንገዳችሁን እንድታገኙ ይፈልጋል፣ እናም መንገዱም አዳኝ ነው።[5] እግዚአብሔር ስለልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ እንድትማሩ እና የመለኮታዊ ደቀ መዝሙርነት መንገድን በመከተል የሚመ ጣውንታላቅ ሰላም እና ደስታ እንዲያጋጥማ ችሁ ይፈልጋል።

ውድ ጓደኞቼ፣ መፈተን ለሚፈልግ ማንም እያንዳንዱ ወንድ፣ ሴት፣ እና ልጅ በጥንት ቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ የሚገኝ በእግዚአ ብሔር ማረጋገጫ የተሰጠው ቀጥተኛ ፈተና ይህ ነው፥

*መጀመሪያ፣* የእግዚአብሔርን ቃላት መፈተሽ አለባችሁ። ይህም ማለት ቅዱሳት መጻህፍትን ማንበብ እናበዳግም ስለተመለሰው ስለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌም የጥንትና የዚህ ዘመን ነቢያትን ቃላት ለመጠራጠር ወይም ለመተቸት ሳይሆን እውነትን ለማግኘት ባለ ቅን ፍላጎት ማጥናት ማለት ነው። የሚሰማች ሁን ነገሮች አሰላስሉ፣ እናም አዕምሮአችሁ እውነትን እንዲቀበሉ አዘጋጁ።[6] "ለማመን ከዚህ የበለጠ ለመፈለግ ባትችሉም ለቃላቴ በውስጣችሁ [ለእግዚአብሔር ቃል] ትንሽ ቦታ ለመስጠት እስከምትችሉ ይህ ፍላጎት በእናንተ ይስራ።"[7]

*ሁለተኛ፣* ማሰብ፣ ማሰላሰል፣ እናም ያለፍርሀት ለማመን መጣር፣[8] እናም ከአዳም ጊዜ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ቤተክርስቲያኑን ለመምራት እና እኛን ወደ እርሱ የምንመለስበ ትን መንገድ ለማግኘት እንዲረዱን ነቢያትን፣ ባለራዕያትን፣ እና ገላጮችን በመስጠት ጌታ ለልጆቹ ምን ያህል መሀሪ እንደነበረ ምስጋና መሰማት ያስፈልጋችኋል።

*ሶስተኛ* የሰማይ አባትን፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እውነታነትን ለእናንተ እንዲያሳይ መጠየቅ አለባችሁ። በቅን ልብ እና በእውን ሀሳብ፣ በክርስቶስ እምነት እያላችሁ ጠይቁ።[9]

በአዳኝ ለእኛ የተሰጠ *አራተኛም* ደረጃ አለ፥ "ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል።"[10] በሌላም አባባል፣ የወንጌል መሰረታዊ መርሆ ችን ለማረጋገጥ ስትሞክሩ፣ መጀምሪያ በእነዚህ መኖር አለባችሁ። የወንጌል ትምህርትን እና የቤተክርስቲያን ትምህርትን በህይወታችሁ ላይ ፈትኑት። በእውን ሀሳብ እና በእግዚአብ ሔር በሚጸና እምነት ይህን አድርጉ።

እነዚህን ነገሮች ካደረጋችሁ፣ በመንፈስ ቅዱስ እውነትን እንደሚያሳያችሁ በቃሉ በታ ሰረው[11] በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አላችሁ። በጭለማ ለመመልከት እና በስጋዊ አይን ለመ ረዳት በማይቻለው መታሰብ ከሚቻለው በላይ የሆነውን አስገራሚ እይታ ምስክር እንድትሆኑ ይፈቅድላችኋል።

ደረጃዎቹ ከባድ ናቸው ወይም ጥረቱን ለማድረግ ዋጋ የላቸውም የሚሉ አንዳንዶች ይኖራሉ። ነገር ግን ይህ የወንጌል እና የቤተ ክርስቲያኗ የግል ምስክርነት በህይወታችሁ ለማግኘት ከምትችሉት በላይ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው። በዚህ ህይወት የሚባርካችሁና የሚመራችሁ ብቻ ሳይሆን፣ ይህም በዘለአለም በሚኖራችሁ ህይወት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል።

### የመንፈስ ነገሮችን ለመረዳት የሚቻለው በመንፈስ ብቻ ነው

የሳይንስ ተማሪዎች በስነ-ፍጥረት ውስጥ ያሉትን በሙሉ በስፋት ለመረዳት ቴክኖሎጂ የሰለጠነ ሆኖ ሙሉ እውነትን ለመረዳት እን ዲችሉ ታላቅ ብርሀኖችን ለመሰብሰብ ይታገሉ ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለመንፈሳዊ እውቀት ተመሳሳይ መሰረታዊ መርሆ አስተምሮ ነበር። ለቆሮንጦስ ሰዎች እንዲህ ጽፎ ነበር፣ "ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመ ንፈስም የሚመረመሩ ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም።"[12]

በሌላም አባባል፣ የመንፈስ እውነትን ለማወቅ ከፈለጋችሁ፣ ትክክለኛውን መሳሪያ መጠቀም አለባችሁ። መንፈሳዊ እውነቶችን ይህን ለመመልከት በማይችሉ መሳሪያዎች ለመረዳት አትችሉም።

አዳኝ በዚህ ቀን እንደነገረን፣ "ከእግዚ አብሔር የሆነው ብርሀን ነው፤ እና ብርሀንን ተቀብሎ በእግዚአብሔር የሚቀጥል፣ ተጨማሪ ብርሀንን ይቀበላል፤ እናም ብርሀኑም ፍጹም እስከሆነው ቀን ድረስም እየጨመረ ይበራል።"[13]

ልባችንን እና አዕምሮአችንን ወደ እግዚ አብሔር በተጨማሪ ዞር ስናደርግ፣ ተጨማሪ የሰማይ ብርሀን በነፍሳችን ላይ ይፈሳል። እናም በፈቃድ እና በትጋት ብርሀንን በምንፈልግ በት በእያንዳንዱም ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር ተጨማሪ ብርሀን ለመቀበል ዝግጁ እንደሆንን እናመለክትለታለን። ቀስ በቀስም፣ የደበ ዘዙ፣ ጥለማ፣ እና የራቁ የመሰሉት ነገሮች ግልጽ፣ ብሩህ፣ እና የምናውቃቸው እየመሰሉ ይመጡልናል።

እንደዚህም፣ ከወንጌል ብርሀን ራሳችንን ካስወገድን፣ ወደኋላ ስንመለከት እና ወንጌል እውነት እንደሆነ ለምን አምነን እንደነበር ለመረዳት እስከማንችል ድረስ የእኛም ብርሀን በአንድ ቀን ወይም በአንድ ሳምንት ሳይሆን ቀስ በቀስ እየደበዘዘ ይመጣል። የድሮ እውቀታችን ሞኝነት ይመስሉናል ምክንያቱም በአንድ ጊዜ ግልጽ የነበረው እንደገና የደበዘዘ እና የራቀ ሆኖአልና።

ለዚህ ነው የወንጌሉ መልእክት ለሚሞቱት ሞኝነት ነው፣ "ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአ ብሔር ኃይል ነውና" ብሎ ጳውሎስ በተደጋ ጋሚ ያለው።[14]

### የሚመዘንበት ፈተና የለም

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሁሉም አይነት ምስክርነት ላላ ቸው ሰዎች ቦታ ነች። ምስክራቸው እርግጠኛ እና በውስጣቸው ብሩህ የሆነላቸው አንዳንድ የቤተክርስቲያኗ አባላት አሉ። ለራሳቸው ለማወቅ አሁንም የሚጥሩ ሌሎችም አሉ። ቤተክርስቲያኗ፣ ምስክራችን ምን ያህል ጥልቅ ወይም ከፍተኛ ቢሆንም፣ ሁሉም በአንድነት አብረው የሚመጡባት ቤት ነች። በምንሰ በሰብበት ቤት በር ላይ "ምስክራችሁ ይህን ያህል እረጅም መሆን አለበት" የሚል ምንም ምልክት እንዳለ አላውቅም።

ቤተክርስቲያኗ ለፍጹም ሰዎች ብቻ አይደ ለችም፣ ነገር ግን ይህችም ለሁላችንም "ወደ ክርስቶስ [የምንመጣባት]፣ እናም በእርሱም ፍፁማን [የምንሆንባት]" ነች።[15] ቤተክርስ ቲያኗ ለእናንተ እና ለእኔ አይነት ሰዎች ናት። ቤተክርስቲያኗ የመለያያ ወይም የመተቺያ ቦታ ሳትሆን የመቀበያና የመንከባከቢያ ቦታ ናት። ይህችም ለመለኮታዊ እውነት የግል ፍተሻች ንን ስናደርግ እርስ በራስ ለማበረታታት፣ ከፍ ለማድረግ፣ እና ለመደገፍ የምንሞክርበት ቦታ ነች።

በመጨረሻም፣ ሁላችንም በደቀመዛሙር ትነት መንገድ ስንጓዝ የእግዚአብሔርን ብርሀን የምንፈልግ መንፈሳዊ ተጓዦች ነን። ምን ያህል ብርሀን እንዳለን ወይም እንደሌለን እርስ በራስ አንኮነንም፤ ነገር ግን ብረሀንን በሙሉ ግልጽ፣ ብሩህ፣ እና እውነት እስከሚሆን ድረስ እርስ በርስ እንንከባከባለን እናም እንበረታታለን።

ለሁሉም የተገባ ቃል ኪዳን

ምስክርነትን ማግኘት የደቂቃ፣ የሰዓት፣ ወይም የቀን ስራ እንዳልሆነ እንወቅ። አንድጊዜ የሚደረግና የሚፈጸም አይደለም። የመንፈስ ብርሀንን የመሰብሰብ ስራ የህይወት ሙሉ ፍለጋ ነው።

የህያው የእግዚአብሔር ልጅ እና በዳግም የተመለሰችው ቤተክርስቲያኑ፣ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ ምስክራችሁ እንደፈለጋችሁት ወዲያው የሚ መጣ ላይሁን ይችላል፣ ነገር ግን ይህን ቃል እገባላችኋለሁ፥ የእናንተ ክፍል ከፈጸማችሁ፣ ይመጣል።

እና ይህም አስገራሚ ይሆናል።

መንፈሳዊ እውነት ልባችሁን እንደሚሞላ እና በመንፈሳችሁ ብርሀን እንደሚያመጣ ቃል እገባላችኋለሁ። ንጹህ እውቀትን ከአስደናቂ ደስታናከሰማያዊ ሰላም ጋር ይገልጽላች ኋል። ይህም በመንፈስ ቅዱስ ሀይል በኩል አጋጥሞኛል።

እንደ ጥንት ቅዱሳት መጻህፍት ቃል ኪዳን፣ ለመናገር የማይቻለው የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት የቤዛ ፍቅር መዝሙርን እንድትዘምሩ፣[16] አይናችሁን ወደ ሰማይ ከፍ እንድታደርጉ፣ እና ድምጻችሁን ከሁሉም በላይ የሆነውን፣ መሰደጃችሁን፣ ተስፋችሁን፣ ጠባቂያችሁን፣ አባታችሁን እግዚአብሔርን ለማሞገስ ከፍ እንድታደርጉ ያደርጋች ኋል። አዳኝ ከፈለጋችሁ፣ እንደምታገኙ ቃል ገብቷል።[17]

ይህም እውነት እንደሆነ እመሰክራለሁ። የእግዚአብሔርን እውነት ከፈለጋችሁ፣ አሁን እንደ ደበዘዘ እና እንደራቀ የሚመስለው ቀስ በቀስ በእግዚአብሔር ጸጋ ብርሀን ይገለጻል እናም ይጠራል እናም ወደልባችሁ ይቀርባል። በሰው አይን ለመታየት የማይታሰበው፣ ግርማ ያለው መንፈሳዊ እይታም ለእናንተ ይገለጻል።

ይህ መንፈሳዊ ብርሀን እያንዳንዱ የእግዚ አብሔር ልጅ ሊደርስበት የሚችል እንደሆነ ምስክሬ ነው። አዕምሮአችሁን ያብራራል እናም ለልባችሁ መፈወስን እና ለቀኖቻችሁ ደስታን ያመጣል። ውድ ጓደኞቼ፣ የምትፈል ጉበትን ጊዜ አታዘግዩ እናም ስለእግዚአብሔር መለኮታዊ ስራ፣ እንዲሁም ስለብርሀን እና እውነት ስራ፣ ያላችሁን የግል ምስክርነት አጠናክሩ።

ስለብርሀን እና እውነት ያላችሁ የግል ምስክር እናንተንና የእናንተን ትውልድ በዚህ ስጋዊ ህይወት በመባርክ ብቻ ሳይሆን፣ ግን ይህም ከእናንተ ጋር በዘለአለም በሙሉ፣ እን ዲሁም መጨረሻ በሌላቸው አለማት ውስጥ፣ አብሯችሁ ይገኛል። ስለዚህ የምመሰክረው እና በረከትን የምሰጣችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፣ አሜን።


ማስታወሻዎች

1. ሙሴ 1፥33
2. ማርሲያ ባርቱሲአክ፣ The Day We Found the Universe (2009)፣ xii ተመልከቱ። ስለ መጨረሻ ውሳኔዎቻችን ልበ ሙሉ መሆን መቻላችን ለእኔ ሁል ጊዜ ያስደንቃል ። አንዳንድ ጊዜ ልበ ሙሉነታችን ታላቅ ሆኖ ሁሉም እውነት ያለን ይመስለናል። ለምሳሌ፣ “በአስራ ዘጠኝ መቶ አመታት መጨረሻ ላይ የአሜርካ የከዋክብቶች ጥናት ዲን የነበረው ሲሞን ኒውኮምብ ከዋክብቶችን የሚያጠኑበት በሚመረቅበት ጊዜ በ1877 (እ.አ.አ) እንዳስመለከተው ‘የከዋክብቶችን ጥናት በሚመለ ከት. . .የእውቀታችንን መጠን ላይ ለመድረስ በፍጥነት እየሄድን እንደሆነ ይመስላል። . . . ውጤቱም ከዋክብት የሚያጠኑትን ትኩረት የያዘው ስራ የአዲስ ነገሮችን ማግ ኘት ሳይሆን አሁን የታወቁትን ነገሮች ማብራራት ነው’ ” (ባርቱሲአክ፣ xv)።
3. በሙሴ 1፥33፣ 35 ያለውን “በቅርብ” ከተገኙት ነገሮች ጋር በማነጻጸር ማሰብ የሚያስደንቅ ነው። በታላቁ ዋጋ እንቁ ውስጥ የሚገኘው የሙሴ መፅሐፍ ለነቢዩ ጆሴፍ ስሚዝ የተገለጸው በሰኔ 1830 (እ.አ.አ)፣ ኤድውን ሀብል በሩቅ የሚገኙ የከዋክብት ክምችቶችን እንዳገኘ ከማስተዋ ወቁ ከአንድ መቶ አመት በፊት ነበር።
4. ለምሳሌ፣ የሀብል ርዕስ የፎቶዎች አዳራሽን በ heritage.stsci.edu/gallery/gallery.html ተመልከቱ።
5. ’ ዮሀንስ 14፥6 ተመልከቱ
6. 3 ኔፊ 17፥3 ተመልከቱ
7. አልማ 32፥27
8. ትምህርት እና ቃል ኪዳን 67፥3 ተመልከቱ።
9. ሞሮኒ 10፥3–5 ተመልከቱ
10. ዮሀንስ 7፥17፤ ደግሞም መዝሙረ ዳዊት 25፥14፤ ዮሀንስ 3፥21 ተመልከቱ።
11. ትምህርት እና ቃል ኪዳን 82፥10 ተመልከቱ።
12. 1 ቆሮንቶስ 2፥14
13. ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 50፥24
14. 1 ቆሮንቶስ 1፥18
15. ሞሮኒ 10፥32፤ ደግሞም ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 20፥59 ተመልከቱ።
16. አልማ 5፥26 ተመልከቱ።
17. ትምህርት እና ቃል ኪዳን 88፥63 ተመልከቱ።



© 2014 በ Intellectual Reserve, Inc. መብቶቹ በህግ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ) ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/14 (እ.አ.አ)


*Visiting Teaching Message, November 2014*. Amharic. 10871 506 ትርጉም